

# ሕፃኑ ኢየሱስ

* መልካሚቱና ጭምቲቱ ማርያም በናዝሬት ከተማ ትኖር ነበር። አናጢ ለነበርው ለዮሴሰፍ እጮኛው ነበረች። ከዕለታት አንድ ቀን መላኩ ገብርኤል ኀበኛትና ወንድ ልጅ እንደምትወለድ ከነገራት በኋላ የልጇ ስምም ኢየሱስ መባል እንዳለበት ይነግራታል። መንፈስ ቅዱስ ከእርሷ ጋር እንደሆነና የምትወልደው ልጅም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ገለፀላት።

* ማርያምና ዮሴፍ ተጋብተው ነበር። አንድ ቀን ወደ ቤተልሔም ለሕዝብ ቆጠራ ተጓዙ። በጣም ረጅም ጉዞ ነበር። ቤተልሔም እንደደረሱም ለእንግዳ ማረፊያ ቦታ ስላጡ በከብቶች ግርግም ለማረፍ ተገደዱ። ሕፃኑም በዚያ ምሽት ተወለደ። መላኩ ገብርኤል እንዳላቸውም ኢየሱስ ብለው ስም አወጡለት።

* በዚያኑ ሌሊትም መልአክ በሌላ ስፍራ ለነበሩ እርኞች ተገለጠላቸው። በዙሪያቸውም ደማቅ ብርሃን አንፀባረቀባቸው።መልአኩም "ኢየሱስ የተባለው መድኃኒት ዛሬ ምሽት ተወለደ።" እረኞቹም ኢየሱስን ለማየት ሄዱ። በከብቶች ግርግም ውስጥም አገኙት።

* የምስራቅ ጠቢባንም ኮከብ እየመራቸው ኢየሱስን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ንጉስ ሄሮድስም እርሱም ለአይሁድ ንጉስ ሊሰግድለት ስለሚፈልግ እንዳገኙት ለእርሱም ያለበትን ቦታ እንዲነግሩት ለመናቸው። (እርሱ ግን ዙፋኔን የሚቀናቀን ሌላ ንጉስ ተወልዶአል የሚል ስጋት ስለነበረበት እንጂ ለተወለደው ለአዲሱ ሕፃን ሊሰግድለት ፈልጎ አይደለም።)

የምስራቅ ጠቢባንም ኢየሱስን በቤተልሔም አገኙት። ሰገዱለትም። ወርቅ፣ ከርቤና እጣንም በስጦታ አበረከቱለት።

* ኢየሱስ አስራ ሁለት ዓመት ሲሞላው ማርያምና ዮሴፍ የፋሲካ በዓልን ለማክበር ወደኢየሩሳሌም ይዘውት ሄዱ። ወደቤት ሲመለሱም እጅግ በጣም ብዙ ተጓዦች ስለነበሩ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እንዳልመጣ አልተረዱም ነበር። እርሱን እየፈለጉ ወደኋላ ሲመለሱ እርሱ በቤተመቅደስ ውስጥ ከሕግ መምህራንና ከአዋቂዎች ጋራ ሲወያይ አገኙት።

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው " በአባቴ ቤት የአባቴን ስራ መስራት እንዳለብኝ አታውቁምን?"

ወደኢየሩሳሌም አብሯቸው ተመሰለ። ይታዘዛቸውም ነበር። ኢየሱስ በጥበብ፣ በቁመትና በእግዚአብሔር ሞገስ ያድግ ነበር።

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ የሕፃንነት ወራት ታሪክ የሚgገኘው በአዲስ ኪዳን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ነው።

http://gardenofpraise.com